በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን


# ቅርስን ለማሰባሰብ የተዘጋጀ መመሪያ

## ቁጥር 762/2013


ሐምሌ 2005ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ቅርሶች በአግባቡ ተጠብቀው ለሳይንስና ለምርምር፣ ለኤኮኖሚያዊ ልማትና ለባህል እድገት የጎላ አስተዋፅኦና ጠቀሜታ ሊያበረክቱ በሚችሉበት መንገድ በባህል ተቋማትና ማዕከላት በማሰባሰብ ማደራጀት ተገቢ በመሆኑ፣

ምትክ የሌላቸውንና የሕዝቦቻችንን ማንነት ዓይነተኛ መገለጫዎች የሆኑ የታሪክና የባህል ቅርሶችን በማሰባሰብ ከማንኛውም ዓይነት ጉዳትና ጥፋት በማዳን ለትውልድ ማቆየት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ሀገራዊ ጉዳይ ስለሆነ፣

የአንድን የቅርስ ስብስብ ማእከል የቅርስ ክምችት በተገቢው ዓይነትና መጠን በማሳደግ ሀገራዊ ደረጃውን እንዲጠብቅ ለማድረግ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የተጠናከረ የቅርስ ማሰባሰቢያ ሥርዓት መዘርጋትና የአፈፃፀም ስልት በመቅረፅ ሥራ ላይ ማዋል በመሆኑ፣

የቅርስ ክምችቶች ስፋት ባለው ብሔራዊ ተዋፅኦ ላይ ተመስርቶ ቅርሶችን ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

**1. አውጭው ባለሥልጣን፤**

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**2. አጭር ርዕስ፤**

ይህ መመሪያ ቅርስን ለማሰባሰብ የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**3. ትርጓሜ፤**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ካልተሰጠው በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አነቀፅ 3 የተሰጠው ትርጉም ለዚህ መመሪያም ያገለግላል፡፡ በተጨማሪ፡-

ሀ. **ቅርስ ማሰባሰብ፡**

በቅርስ ስብስብ ማእከሎች የቅርስ ማሰባሰቢያ ስርአት መሰረት የተለያዩ ቅርሶችን ማሰባሰብና ወደ ስብስብ ክፍል ማስገባት ነው፣

ለ. **የስብስብ ክፍል፤**

የተለያዩ ቅርሶች ተሰባስበው የሚጠበቁበት፣ እንክብካቤ የሚደረግበት፣ የሚደራጁበትና ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ዝግጁ የሚሆኑበት ክፍል ነው፡፡

ሐ. **ቅርሶችን በስጦታ ማሰባሰብ፤**

በራሳቸው ፍላጎት ሊለግሱ ከሚችሉ አካላት ወይም ግለሰቦች ቅርሶችን በስጦታ ማሰባሰብ ማለት ነው፡፡

መ. **ቅርሶችን በግዢ ማሰባሰብ፡**

የታሪካዊ ፤ የስነጥበብ፣ የኢትኖግራፊና የንፅፅራዊ ሥነ አካል /ኮምፓራቲቭ አናቶሚ/ቅርሶችን የቅርስነት እሴት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በግዢ ማሰባሰብ ማለት ነው፡፡

ሠ. **ቅርሶችን በአደራ ማሰባሰብ፡**

የቅርስ ባለይዞታዎች ከስብስብ ማእከሎች ጋር በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት በአደራ ተረክበው በተወሠነ የጊዜ ገደብ ቅርሶቻቸውን የሚያስቀምጡበት ሂደት ነው፡፡

ረ. <u>ቅርሶችን በውሰት ማሰባሰብ</u>፤

የስብስብ ማእከሉ ቅርሶችን ለዐውደ ርዕይ፤ ለጥናትና ምርምር እና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች በሚፈልግበት ጊዜ ከአዋሹ ጋር በሚደረግ ስምምነት መዋስ ማለት ነው፡፡

ሰ. <u>ቅርሶችን በውርስ ማሰባሰብ</u>፤

ቅርሶች በሙዚየም መጠበቃቸው ሲታመንበት ወይም በህገ ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ወይም የቅርስ ባለይዞታዎች ተገቢ እንክብካቤ ሳያደርጉ ሲቀር ወይም ቅርሶችን የሚወርስ ወይም የሚረከብ አካል ሣይኖር ሲቀር መውረስ ማለት ነው፡፡

ሸ. <u>ቅርሶችን በልውውጥ ማሰባሰብ</u>፤

አንድ ቅርስ እንደየስብስብ ክፍሉ አይነት ከሚፈለገው ቁጥር በላይ ሲሆን ከሌሎች ግለሰቦች ወይም ተቋማት ጋር በሚደረግ ስምምነት ቅርሶችን መለዋወጥ ማለት ነው፡፡

ቀ. <u>ቅርሶችን በጥናትና ምርምር ማሰባሰብ</u>፡

በመመሪያው መሰረት ቅርሶችን በመስክ አሰሳ እና በቁፋሮ ማሰባሰብ ማለት ነው፡፡

በ. <u>ከሀገር ውጪ ያሉ ቅርሶችን በማሰባሰብ</u>፤

በተለያዩ ጊዜያት በህገ ወጥ መንገድ ከሀገር የወጡ ቅርሶች ከሚገኙባቸው ሀገራት ሲመለሱ ወደ ስብስብ ማስገባት ማለት ነው።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ቅርሶችን የማሰባሰብ ስልቶች</u>

**4. በስጦታ፤**

1. የስብስብ ክፍሎች ቅርሶችን በስጦታ ሊያበረክቱ የሚችሉ አካላትን ለማነሳሳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራሉ፤
2. የስብስብ ክፍሉ በስጦታ የሚያገኘውን ቅርስ የቅርስነት መስፈርት ማሟላቱንና መረጃ ያለው መሆኑን በቅድሚያ በባለሙያ በማረጋገጥ መረጃውንም በቅርስ መረከቢያ ቅፅ ላይ በዝርዝር በማስፈር ይረከባል፣
3. ቅርስን በስጦታ የሚያበረክት አካል ከተረካቢው የምስጋና ሰርተፍኬት ይሰጠዋል፡፡
4. በስጦታ ወደ ስብስብ ክፍሎች የሚገቡ ቅርሶች ሕጋዊ የስጦታ አፈፃፀም ስርአትን የተከተሉ ሆነው በማንኛውም ሁኔታ ክፍያ ወይም መተኪያ ሊጠየቅባቸው አይችልም፡፡
5. በጊዜያዊ አውደ ርዕይ ለእይታ የቀረቡና በሥራዎቹ ባለቤት የሚበረከቱ ውጤቶች ወደ ስብስብ ክፍል እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

## 5. በግዥ

1. በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቅርስ ግዥ የተገለጋዮችንና የስብስብ ክፍሎችን ፍላጎት በማጥናት ይከናወናል፡፡
2. የታሪክና የባህል ቅርስ ካለው ልዩ ይዘትና ባህርይ የተነሳ ግዥው በመንግስት የግዢ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 649/2001 በተመለከተው መሠረት ያለጨረታ ይፈፀማል፡፡
3. ቅርሶችን በሽያጭ የሚያቀርቡ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ባለቤትነታቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃ ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡
4. በአደራ ተቀምጦ የቆየን ቅርስ በብሔራዊ ወይም በክልል ደረጃ ይዞ በስብስብ ማእከል ክምችት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበትና በሚኒስቴሮች ም/ቤት ካሳው ሲወሠን ወይም ቅርስን በአደራ ያስቀመጠ ባለይዞታ የአደራ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት መሸጥ ከፈለገ የስብስብ ክፍሉ ሊገዛ ይችላል፤

## 6. በአደራ

1. የስብስብ ክፍሉ የአደራ ሰጪውን ማመልከቻ በመቀበል ቅርሱን ከቦታው ሄዶ በማየት ስለነባራዊ ሁኔታው መረጃ ይሰበስባል፣
2. ማንኛውም የቅርስ ባለይዞታ በስብስብ ክፍሉ ቅርሶችን ማስቀመጥ የሚችለው ከ5 አመት ላልበለጠ ጊዜ ሲሆን በአደራ ያስቀመጠውን ቅርስ መውሰድ የሚችለውም ከክፍሉ ጋር የተስማማበትን የጊዜ ገደብ ሲያጠናቅቅ ብቻ ነው፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ቅርስን በአደራ ማስቀመጥ የሚፈልግ የቅርስ ባለይዞታ ስምምነቱን ለአንድ ጊዜ ብቻ ለ2 ዓመት ማደስ ይችላል፡፡ ይህንን ካላደረገ ግን የስብስብ ክፍሉ ቅርሱን ሊወርስ ይችላል፤
4. የስብስብ ማእከሉ በአደራ ለሚያስቀምጣቸው ቅርሶች ብዛትና ዓይነት መመዘኛ ያወጣል፡፡
5. የስብስብ ማእከሉ ማንኛውንም ዓይነት ቅርስ በአደራ ሲቀበል በስምምነት ቅጽ ላይ መረጃዎቹንና የአደራ አስቀማጩን መብትና ግዴታ በዝርዝር በሚገልፅ ውል ከአስረካቢው ወገን ጋር በመፈራረም ይረከባል፡፡
6. የስብስብ ማእከሉ በአደራ የሚቀበላቸውን ቅርሶች ከአደራ አስቀማጩ ጋር በሚደረግ ስምምነት ላይ በመመስረት ቅርሶችን ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊጠቀምባቸው ይችላል፡፡

## 7. በውሰት

አንድ ቅርስ በውሰት መልክ ሲሰባሰብ፡

1. ለተወሰነ ጊዜ ለዐውደ ርዕይ፣ለጥናትና ምርምር፣ለትምህርትና ለመዝናኛ አገልግሎቶች ይውላል፣

2. ቅርሱ በውሰት የሚቆይበት የጊዜ ገደብ በአዋሹና በተዋሹ ስምምነትና በቅርሱ የውሰት አስፈላጊነትና አላማ ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ይሆናል፣

3. ቅርሱ በውሰት ከመሰብሰቡ በፊት ሁሉንም የዋስትና ሁኔታዎች በተመለከተ በአዋሹና በስብስብ ማእከሉ መካከል የውል ስምምነት መኖር አለበት፡፡ በስምምነቱም ላይ ኃላፊነቱን የሚወስደው አካል ተለይቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 8. በውርስ

1. በህገ ወጥ መንገድ የተያዘን ወይም ሲዘዋወር የተገኘን ቅርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ወደ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለ፤ሥልጣን የማስገባት ሙብት ይኖረዋል፤
2. አንድ ቅርስ በግለሰብ እጅ ያለ ሆኖ ባለይዞታው ከዚህ አለም በሞት ቢለይና እና ሕጋዊ ወራሽ ባይኖር ቅርሱን ባለሥልጣኑ ይወርሳል፡፡
3. በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 25 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 በተደነገገው መሰረት በስብስብ ማዕከል መጠበቁ የታመነበት ቅርስ ወይም ተገቢው ጥበቃ፣ጥገናና እንክብካቤ ያልተደረገላቸውን ወይም ለብልሽት የተጋለጡትን ወይም ለሌላ ሕገወጥ አገልግሎት የዋሉ ቅርሶችን ባለስልጣኑ ሊወርስ ይችላል፡፡

## 9. በልውውጥ

1. በታሪካዊ ወይም በሥነ-ጥበብ ወይም በኢትኖግራፊ ስብስብ ማእከሎች ውስጥ አንድ የቅርስ አይነት እንደየስብስቦች የቅርሶች ዓይነት ከሚፈለገው ቁጥር በላይ ሆኖ ሲገኝ ከሌሎች የስብስብ ማእከሎች ወይም ተቋማት ጋር በመነጋገር ቅርሶችን መለዋወጥ ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ስር ከሚፈለገው ቁጥር በላይ የሚለው እንደ ስብስብ ክፍሉ እና የቅርሱ ባህሪ ታይቶ በሚወጣው የሥራ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

## 10. ከመስክ በጥናትና ምርምር

1. በባለስልጣኑ የጥናትና ምርምር መመሪያ መሰረት ፈቃድ በተሰጣቸው የተለያዩ አጥኚዎች በመስክ አሰሳ እና በቁፋሮ የተሰባሰቡ የተለያዩ ቅርሶችን ወደ ስብስብ ማእከሉ እንዲገቡ ይደረጋል፣
2. በግንባታ ወቅት በአጋጣሚ የተገኙና በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 41 መሰረት አስፈላጊው ሁኔታ የተከናወነላቸው ቅርሶችም ወደ ስብስብ ክፍል እንዲገቡ ይደረጋል፡፡
3. ከመስክ በጥናትና ምርምር የሚሰባሰቡ ቅርሶች በዋነኛነት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡
   3.1 የጥንተ ዓለም ፍጥረት ቅሪተ አካል
   3.2 የአርኪዮሎጂ

3.3 የጥንተ አለም የሰው ዘር ቅሪት አካል

3.4 የሶስዮሎጂና ባህላዊ ስነ ሰብዕ

## 11. ከሀገር ውጪ የሚመለሱ ቅርሶችን ማሰባሰብ፤

1. በውጪ ሀገር የሚገኙ ቅርሶችን በተመለከተ የተገኘው አስፈላጊው የሠነድና ተዛማጅ መረጃ ቅርሶችን ለማስመለስ ሥልጣን ላለው አካል ይተላለፋል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መረጃቸው የተሰበሰቡና አለም ዓቀፍ ህጎችን በመከተልና ቅርሶቹ ከሚገኙባቸው ሀገራት መንግስታት ጋር ግንኙነት በማድረግ የተመለሱት ቅርሶች ወደሚመለከታቸው የስብስብ ክፍሎች እንዲገቡ ይደረጋል፣
3. ዋና ቅርሶችን ማግኘት ወይም ማስመለስ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ቅጅዎቻቸውን በማሰራት ወደ ስብስብ ክፍሉ የሚገቡበት መንገድ ይፈለጋል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**<u>የሚሰበሰቡ ቅርሶች መመዘኛ መሥፈርቶች</u>**

## 12. ታሪካዊ ቅርሶች

መረጃ ያላቸው፣ በታሪካዊ ይዘታቸው የጐላ ድርሻ የሚያበረክቱ ሆነው፡-

1. ከቁፋሮ ውጭ የተገኙና ቀደምትነት ያላቸው ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሐስ ወይም ከሌሎች ቁሶች የተሰሩ ገንዘቦች፣
2. በተወሰነ የታሪክ ወቅትና ሁኔታ በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተፈፀሙ ክንዋኔዎች በሀገራት መሪዎች፣በጦር አበጋዞች፣ በሀይማኖት አባቶች፣ በጠቢባንና በሌሎችም ታላላቅና ታዋቂ ሰዎች ዘንድ አገልግሎት ላይ የዋሉና ለተፈፀመው ክንዋኔ በአስረጅነት መወሠድ የሚችሉ ቅርሶች፡
3. ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሐስ ወይም ከሌላ ቁስ የተሠሩ ሆነው ረዘም ያለ እድሜ ያላቸው የነገሥታት ወይም የሀይማኖት መሪዎች ወይም የሌሎች ታላላቅ ሰዎች ስም ወይም ምስል የተቀረፀባቸው እንደ ፅናፅል ወይም ሰን ወይም ብርት ወይም መስቀሎች ወይም ስዕሎች ወይም የመቋሚያ መጨበጫዎች ወይም አትሮንሶች የመሳሰሉት ቅርሶች፡
4. ከውጪ ሀገር መንግሥታት ወይም የልዑካን ቡድኖችና ከመሳሰሉት ለኢትዮጰያ ታላላቅ ሰዎችና ልዩ ልዩ ተቋማት የተበረከቱ የወዳጅነት፣ የክብርና የመታሰቢያ ዕቃዎች፤
5. የብራና መፃሕፍት ፡

5.1 ማንኛውም ከብራና የተዘጋጀ መፅሐፍ፣ በስድ ንባብ ወይም  በግጥም በአማርኛና  በግዕዝ ወይም በአረብኛ ወይም በሌሎች ቋንቋዎች ተጽፎ የሚገኝ ፅሁፍ፣

5.2  እንደ መጽሐፍ የተጠረዘ የአስማት ወይም የሥዕል ጽሑፍ ወይም ሥንክሣር፣

5.3  በብራና ላይ የተጻፉ ታሪካዊ ሰነዶች ወይም ክታቦች ወይም ገድሎች ወይም ዜና  መዋዕሎች ወይም ሌሎችም  የሐረግ ጌጥና ሥዕል ያለባቸው ጽሑፎች

5.4  ቀደም ሲል ያልተለመደና አዲስ የብራና ሥራ ውጤት የሆነ፣

## 13. የሥነ ጥበብ፣ቅርሶች

1. መሠረታዊ የሆነ የሥነጥበብ አሠራር ክሕሎትን የተከተለ ሥዕል ወይም ቅርፅ የሆነ፣
2. ሥዕሉ ወይም ቅርፁ የተሠራበት ቁስ ዓይነትና ጥራቱ የቆይታ ጊዜውን ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የማይደበዝዝና የማይሰበር፣
3. ከመፅሔት ወይም ከመፅሐፍ ላይ ኮፒ ሆኖ ያልተሠራና በራስ ፈጠራ ብቻ ላይ የተመሠረተ፣
4. የስነጥበቡ ድርሰት ቅንብር ወጥና ትውልድ ተሻጋሪ ሆኖ በግራፊክስ ወይም በሐውልት ወይም በሚዩራል ወይም በሚክስድ ሚዲያ ወይም በባህላዊና ዘመናዊ ቀለም ቅብና አሣሣል ወይንም በማንኛውም ዓይነት መንገድ የተሰራ፣
5. የብሔር ብሔረሰቦችን ባህል፣ ሀይማኖትን፣ ልማዳዊና ባህላዊ እምነቶችን በጎ ገፅታቸውን የሚያንፀባርቅ ወይም ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ግለሰቦች ስራ የሆነ፣
6. መረጃን ያሟላ ማለትም የባለሙያው ሥም፣ የተሠራበት ቁስ፣ የተሠራበት ዘመን፣ የመሳሰሉት መረጃዎችን የያዘ በስነ-ጥበብ ቅርስነት ይሰበሰባል፣

## 14. የኢትኖግራፊ ቅርሶች

የኤትኖግራፊ ቅርሶች የሀገራችንን  ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ማንነት ፣ ታሪክ ፣ ባህል ፣ እምነት ፣ ወግ ፣ ልማድ፣ አመለካከት ፣ አኗኗራቸውን ገላጭ የሆኑና በህትመት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የተዘጋጁ ወይም በቁስ የሚገኙ ሆነው፡-

1. የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች፣
2. አልባሳትና ጌጣጌጦች፣
3. የጦርና የአደን መሣሪያዎች፣
4. የሙዚቃና የመጫዎቻ መሳሪያዎች፣
5. የዕደ ጥበብ ሥራ ውጤቶች፣
6. ሃይማኖታዊ ባህላዊና ልማዳዊ የበዓላት መከወኛ ቁሳቁሶች፣
7. የማምረቻ መሣሪያዎች የሆኑት ሊሠባሠቡ ይችላሉ፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**15. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**16. ቅጣት**

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

**17. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የሚመለከተው ስልጣን ያለው አካል ሊያሻሽለው መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ ------------ ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሚን አብዱልቃድር

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር

-----------.............ቀን 2005 ዓ፡

አዲስ አበባ